# 7. አባድር-መካኒሳ መስጂድ

«እይ እንግዲህ. . .መካኒሳ ማለት ያች ዛፍ ናት. . .»

*የተመሰረተበት ዘመን*፡- በ1968 አካባቢ

*የሚገኝበት ቦታ*፡- በመካኒሳ አካባቢ፣ (ከሜክሲኮ ሳርቤት፣ ከሳርቤት መካኒሳ መንገድ ላይ፣ ከዋናው አስፓልት በስተግራ ገባ ብሎ የሚታይ)፡፡

## መግቢያ

የመካኒሳ አባድር መስጂድ ሁለገብና የተሟላ እስላማዊ ማዕከል ነው፡፡ በተለይም በዙሪያው በትምህርት ማዕከላት ግንባታ የሚደነቅና ግንባር ቀደምነት ደረጃ ያለው ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ከመስጂዱ በተጨማሪ ዘመናዊ የመስገጃ ቦታዎችን በመስጂዱ ዙሪያ በማስፋፋት የሚደነቅ ተግባር ያለው ነው፡፡ ስለዚህም ይመስላል የመዲናዋ (የአዲስ አበባ) ዲፕሎማቶች በብዛት የሚመርጡትና የሚጠቀሙበት መስጂድ ለመሆን የበቃው፡፡ በተነፃፃሪ ሁኔታ ከሁሉም መስጂዶች በላይ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶችና ታላላቅ እንግዶች በብዛት በመካኒሳ አባድር መስጂድ ይሰግዳሉ-በተለይም በጁመዓና በረመዷን ወር፡፡ እርግጥ የፀጥታው፣ የመረጋጋቱና የደህንነቱ አስተማማኝነትም ሌላው ተመራጭ ካደረጉት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ አባድር መስጂድ በቂ የሆኑ አስተናጋጆችና ደህንነቱን





የሚጠብቁ ዘበኞች. . . ያሉት በመሆኑ ፀጥታው ሁልጊዜም አስተማማኝ ነው፡፡ ለመኪና ማቆሚያም አመቺነት ስላለው ይወደዳል፡፡ ከዋና መንገዶች ብዙ ሳይርቅ፣ በጣምም ሳይቀርብ በጥሩ ተዳፋታማ ቦታ አካባቢ መገኘቱም ለተመራጭነቱና ለፀጥታው የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያደረገ ይመስላል፡፡ ስለሆነም ፀጥታን የሚሹ ብዙ የከተማችን ባለሃብቶች፣ ባለስልጣናት፣ ዲፕሎማቶችና ሌሎች ወደ አባድር መስጂድ መሄድን ይመርጣሉ፡፡ የአባድር መስጂድ ንጽህናው ሌላኛው ውበቱና ብዙዎችን የሚስብበት ዕድገቱ ነው፡፡ ሁልጊዜም ንጹህና ጽዱ ነው፡፡ ለዚህ ንጽህናው የሚገኝበት ቦታ ተዳፋትነት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አድርጎለታል፡፡ በቀላሉ ማጽዳትና እንክብካቤ ለማድረግ ያመቻል፡፡ የግቢው ውስጥ አገልግሎቶች ሁሉ የመሬቱን ተዳፋትነት መሰረት ባደረገ ፕላን የተሰራ በመሆኑ ለውበቱና ለንጽህናው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አስገኝቷል፡፡ ሁሉ ነገር በቀላሉ ወደታች (ወደወንዙ) እንዲፈስና እንዲወርድ የተደረገ ነው፡፡ ሙያ ካለ ሁሉ ተፈጥሮ ለሰው ልጅ አመቺና አስደሳች እንደሆነ ከአባድር መስጂድ ማስተዋል ይቻላል፡፡

*አመሰራረት*፡- በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዘመነ ማብቂያ አካባቢ በአዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ የሀረሪ ተወላጅ ሙሁራን ተሰባስበው ተመካከሩ፡፡ ይህም ለወደፊቱ ልጆቻቸውን የዲን ትምህርት ማስተማሪያ ማዕከልና ተሰባስበው የሚሰግዱበት

መስጂድ እንደሚያስፈልጋቸውና ይህንን ለማሳካት ደግሞ በአንድ አካባቢ መኖር (ቤት መመስረት) የግድ እንደሚል ነበር:: በጊዜው በአዲስ አበባ ብዙ የሙስሊም ህብረተሰብ ስለሌለ ባህላቸውንና ዲናቸውን ጠ ብ ቀ ወ - ለ መ ኖ ር ተሰባስበው መኖርና የሚያስፈልጋቸውን መድረሳና መስጂድ መገንባት እንደሚኖርባቸው ተማምነው ይጨርሳሉ:: በዚህም መሰረት 14/5 ሰዎች በመሰባሰብ በአንድ አካባቢ የመኖሪያ ቤትና መስጂድ ለመገንባት የሚያስችላቸውን እርምጃ ለመውሰድ መዋጮ ማድረግ ይጀምራሉ:: የመዋጮው መጠንም በወር 10 ብር ነበር:: በጊዜው ይህንን ምክክርና ተግባር ከጀመሩት ውስጥ

1. አቶ ዩሱፍ አህመድ ዓሊ (አላህ ይማራቸው)
2. አቶ ረሺድ አህመድ (በሕይወት ያሉ)
3. አቶ አህመድ ሙሐመድ ሸኽ (በሕይወት ያሉ)
4. ክቡር ሙሐመድ አብዱራህማን ሸኽ (ከሀገር ውጭ በሕይወት ያሉ)
5. ኢንጂነር አብዱልሰመድ አህመድ (በድሬዳዋ ያሉ)
6. ሐጂ መህዲ ሽንብሮ (በሕይወት ያሉ)
7. ሐጂ ሙሐመድ ኢብራሂም (በሕይወት ያሉ)
8. ሐጂ ዱሪ አባስ (በሕይወት ያሉ)
9. አቶ ዓሊ ሽሪፍ (በሕይወት ያሉ)
10. ሐጂ አብደላ አደም (በሕይወት ያሉ)





11. ሐጂ አብደላ አብዱልማሊክ (አላህ ይማራቸው)
12. ሐጂ አህመድ ዓሊ (አላህ ይማራቸው). . . ይገኙበታል::

ቀሪዎቹ በመጀመሪያው ሀሣብ ቢኖሩም በተለያዩ ምክንያቶች በሂደቱ ያልቀጠሉ በመሆናቸው ለጊዜው ስማቸውን ማስታወስ ነጋሪያችን አልቻሉም::

እነዚህ ሙሁራን ውሳኔያቸውን አጽንተው መዋጮዋቸውን ካጠናከሩ በኋላ በዚሁ አሁን መስጂዱ ባለበት አካባቢ እያንዳንዳቸው 500 ካ.ሜ የመኖሪያ ቦታ ይገዛሉ:: ለመስጂዱም እንዲሁ 500 ካ.ሜ ጨምረው ይሸምታሉ (በካ.ሜ ሁለት ብር ሂሳብ):: ሁሉም ቤቱን ከገነባ በኋላ መስጂዱም ተጀመረ:: መስጂዱን ለማሰራት የነርሱ አቅም ብቻውን ሲወጣው ስለማይችል በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩትን የሀረሪ ተወላጆችን ማስተባበር ግድ ይል ስለነበር ሁሉም ተሳትፎውን ሊያደርግ በቅቷል:: በዚህም ሙሉ የሀረሪ ተወላጆች ተሳትፎ አሁን ያለው መስጂድ መካከለኛው ዋና ክፍል በ1968 አካባቢ ለመሰራት በቃ::

በዚህ አካባቢ እነዚህ ሰዎች ከመስፈራቸውና መስጂድ ከመገንባታቸው በፊት አካባቢው ጥቅጥቅ ያለ ጫካና ማንም ያልነበረበት ሲሆን እነርሱ ከጀመሩት በኋላ በተለይም መስጂዱ ከተሰራ ወዲህ የሀረሪ ተወላጆች በያሉበት ወደዚህ (መካኒሳ) በመምጣት ቤት ይሰሩ ጀመር:: በሂደትም ዛሬ በመካኒሣ አባድር መስጂድ ዙሪያ አብዛኛው ሙስሊም ነዋሪ የሀረሪ ተወላጆች

ለመሆን ቻለ:: ለዚህም ነው ዛሬ መካኒሳ ሲባል የበርካታ ሀረሪዎች መንደርነትዋ ትዝ የሚለን:: ነዋሪዎቹና መስጂዱ በአካባቢው ቀዳሚና ጥንታዊ እንደመሆናቸው መጠን ስለ አካባቢው «የመካኒሳ» ሥያሜ ከነርሱ የተሻለ የሚያውቅ ሊኖር አይችል ይሆናል ብዬ ለኢንጅነር ሙሐመድ ዩሱፍ ጠይቄአቸው ነበር:: እርሳቸውም «ና ላሳይህ» ብለው ከቢሯቸው ወደ ውጭ ይዘውኝ ወጣን:: «እይ እንግዲህ. . .መካኒሳ ማለት ያች ዛፍ ናት. . .» ብለው በመስጂዱ ቅጥር ግቢ ያለችን ትልቅ ዛፍ በርቀት አሳዩኝ:: ቀጠሉናም «በድሮ ጊዜ አካባቢው በሙሉ በእርሷ አይነት ዛፎች የተሞላ ነበር:: ለዚህም ነው መካኒሳ የተባለው» ሲሉ አስረዱኝ:: የዚህች ዛፍ ሥም መካኒሳ መሆኑ በምን ቋንቋ ነው? ስል ጠየቅኳቸው:: «በኦሮምኛ ይመስለኛል በሱ ነው» ሲሉ መለሱልኝ::

## <u>የመስጂዱ ዕድገትና አሁን ያለበት ደረጃ</u>

ዋናው መስጂድ ያረፈበት 500 ካ.ሜ ቦታ በመጀመሪያ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዘመን የተገዛ ቢሆንም በሂደት በዙሪያው የነበረውን ክፍት መሬት በደርግ ዘመነ መንግስት በማካተት፣ በኢሕአዴግ ጊዜም ከበስተ ምዕራብ ወንዙ ዳር የሚገኘውን ተጨማሪ 5000 ካ.ሜ አካባቢ ከመንግስት በነፃ በማግኘት. . . በአሁኑ ጊዜ በጠቅላላው ከ27,000 ካ.ሜ የማያንስ ሕጋዊ ይዞታ ያለው ማዕከል ነው:: የመስጂዱ ዋና ክፍል





ተጠናቆ መስገድ ከተጀመረበት በኋላ ቀስ በቀስ የተጠቃሚው ቁጥር እየጨመረ መጣ:: የመስጂዱ አስተዳደር መስጂዱ በተጠቃሚው መጠን ብቻ እንዲያድግ ማድረጉ የሚሰጠውን ፋይዳ በማስተንተን በቀኝ ክንፍ ያለውን ክፍል ሰራ:: ቀጥሎም በግራ ክንፍ ያለውን የሴቶች መስገጃና መዋዕለ ሕፃናት ያለበት ባለ ሁለት ፎቅ ክፍሎች በሟቹ ሐጂ. አብደላ አብዱልማሊክ ገንዘብ ሊሠራ ቻለ::

በመስጂዱ የሰጋጆች ቁጥር እጅግ የሚበራከተው ለጁምዓ ሰላት በመሆኑ በግለሰብ በጎ አድራጊዎች በስድስት የተለያዩ ጊዜያት መጠለያዎች ሊሠሩ ችለዋል::

መስጂዱ ለኢማምና ሙአዚን መኖሪያ ቤት ከማሠራቱም በላይ ለዳዕዋ የሚመጡ ጀማዓዎች የሚያርፉበት ክፍልና መታጠቢያ ቤቶችንም ገንብቷል:: እንደዚሁም በሁለት የተለያዩ ሥፍራዎች የውዱዕ ማድረጊያ ቦታ በሰፊው በማዘጋጀቱ ተጠቃሚዎች ወረፋ ሣይበዛባቸው ይስተናገዳሉ:: መስገዱ በይዞታ ባለው ሰፊ ማዕከል ውስጥ የተለያዩ እስላማዊ አገልግሎቶች ያሉ ሲሆን በዋናነትም:-

1. የመስጂድ አገልግሎት የሴቶችንም ጨምሮ ከነ ሙሉ አገልግሎቱ ጋር
2. መዋዕለ ሕፃናት (KG)
3. የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት (ከ1-8ኛ)

4. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (ከ9-10ኛ)

5. ፕሪፓራቶሪ ($10^{+1}$፣ $10^{+2}$) ይገኝበታል::

ይህም በአዲስ አበባ መስጂዶች ታሪክ ታላቅ ደረጃና እመርታ ነው (አላሃምዱሊላህ)::

***የሰጋጅ ብዛት:-*** በአሁኑ ጊዜ መስጂዱ በየቀኑ ከ1500 በላይ፣በየጁመዓው ከ3000 በላይ በማስተናገድ ላይ ይገኛል::

**የተማሪዎች ብዛት:-** በመስጂዱ ቅጥር ግቢ ከኬጂ-$10^{+2}$ ፕሪፓራቶሪ በሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ:: የዲን ትምህርት የሚከታተሉም በርካታ ደረሶች አሉ:: የቁርዓን ማስቀራትና የቁርዓን ማስህፈዝ አገልግሎትም መስጂዱ ይሰጣል::

**ኢማሞች:-**

1. ሸኽ አብዱልሰላም
2. ሸኽ አህመዲን (ስልጤ)
3. ሸኽ አደም ሙሐመድ
4. ሸኽ ኢብራሂም መሐመድ
5. ሸኽ ማህሙድ ኢብራሂም (አሁን ያሉት)
6. ሸኽ ሙሐመድአሚን አህመድ (ምክትል)

**ሙአዚኖች:-**

1. ሸኽ ሀሰን አህመድ
2. ሸኽ አብደላህ ዓሊ





3. ሸኽ አብዱልከሪም አወል (አሁን ያሉት)
4. ሸኽ ሙሐመድ ሰኢድ ( ሁለተኛው)

**ዓሊሞች:-**

1. ሸኽ ሙሐመድአሚን አህመድ (ለ30 ዓመታት ያስተማሩ)
2. ሸኽ ኸድር ሀይደር

**አስተዳደር:-** ኢንጅነር ሙሐመድ ዩሱፍ (የአስተዳደር ኮሚቴ አባል)

**የመረጃ ምንጭ:-**

1. ኢንጅነር ሙሐመድ ዩሱፍ
2. ሸኽ ሙሐመድአሚን አህመድ
3. አቶ አብዱልዋሲዕ ዩሱፍ ዓሊ

**የስልክ አድራሻ:-**

**011-3-71 87 64**